የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፷፭
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 65
ADDIS ABABA, 3rd September, 2024

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፭/፪ሺ፲፮

ለመጀመሪያው ዘላቂና ሁሉን አቀፍ የእድገት ልማት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ…………..………….ገጽ ፲፯ሺ፵፯

**Content**

Proclamation No. 1345/2024

International Development Association Loan Agreement for Financing First Sustainable and Inclusive Growth Development Policy Financing Program Ratification Proclamation………..……..…….......Page 17047

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፭/፪ሺ፲፮**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለመጀመሪያው ዘላቂ እና ሁሉን አቀፍ የእድገት ልማት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የሚውል ሦስት መቶ ሰማንያ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር (፫፻፹ ሚሊዮን ፪፻ሺ. ኤስ.ዲ.አር) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሐምሌ ፳፫ ቀን ፪ሺ.፲፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

**PROCLAMATION No. 1345/2024**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS,** the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to Three Hundred and Eighty Million Two Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 380,200,000) for financing First Sustainable and Inclusive Growth Development Policy Financing Program, was signed in Addis Ababa on 30th day of July, 2024;

ይህንኑ ስምምነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአካሄደው ፩ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለመጀመሪያው ዘላቂና ሁሉን አቀፍ የእድገት ልማት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፭/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሐምሌ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 7618-ET በዚህ አዋጅ ጸድቋል።

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ሦስት መቶ ሰማንያ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር (፫፻፹ ሚሊዮን ፪፻ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its 1st Extra Ordinary Session held on the 31th day of July 2024;

**NOW, THERFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for Financing First Sustainable and Inclusive Growth Development Policy Financing Program Ratification Proclamation No. 1345/2024".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 7618-ET signed in Addis Ababa on 30th day of July, 2024 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to Three Hundred and Eighty Million Two Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 380,200,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

፬. **<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 3rd Day of September, 2024**

**SAHLE WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**